# ትብብር ከማን ጋር? ዓላማውና ልዕለ-ግቡስ?

## ኢትዮጵያን ለማዳንና ሕዝቧን ለመታደግ ኢትዮጵያዊ አስተሣሰብንና እምነትን ይጠይቃል!

*(ክፍል ሁለት - ካለፈው የቀጠለ)*

*ከአያልሰው ደሴ፡- የግል አስተያየት ( ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፪ ሀሽ ፫ ዓ/ም)*

ወደ-ነጥቦቹ ከመሄዳችን በፊት ግን እስካሁን "*በኢትዮጵያ ጉዳይ አያገባንም፣ ትግላችን ኢትዮጵያ ከምትባል 'ቅኝ-ገዥ' ጋር ስለ-ሆነ ከኢትዮጵያውያን ጋር የሚያሰልፈን ምክንያት የለም*" በሚል አቋማቸው ከታወቁትና በአሁኑ ጊዜ "ትብብር" ፈጣሪ ስለሆኑት ድርጅቶች በአጭሩ ማየቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ "የምጣዱ ሣለ የእንቅቡ ተንጣጣ" እንዲሉ ስለ-እነዚኽ ድርጅቶች እነሱ ስለ-እራሣቸው ከሚናገሩት ይበልጥ አንዳንድ ወገኖች በእነሱ ቦታ ሆነው ስለ-እነሱ "በጎ" ጎናቸውንና ለምን ዓላማ እንደ-ቆሙ ሊያስረዱና ለማሣመን ሲቃትቱ ስለ-ሚታይ ዞር ብሎ ድርጅቶቹን እነሱ እራሣቸውን ከሚያዩበት ማዕዘን መቃኘቱ አስፈላጊ ነው ብየ አስባለሁ፡፡

ከሁሉ በፊት ግልጥ መሆን ያለበት ጉዳይ አለ፡፡ በመሠረቱ ድርጅቶች በተደራጁበት የተለያየ መልክ እንዲደራጁ የሆነው በአብዛኛው በአገሪቱ ባለ የወቅቱ ሁኔታ አስገዳጅነትና የዚያም ነፀብራቅ በመሆናቸው እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ ሁሉም የተመሠረቱት በአንድ መልኩ ይሁን በሌላ የሕዝብን ብሶት መሠረት አድርገውና ምላሽ ለማስገኘት የተሻለ አማራጭ ነው ያሉትን መንገድ ተከትለው ነው፡፡ ሕወሓትም ሆነ ኦነግ፣ ሽዓብያም ሆነ ኦብነአግ፣ ወዘተ.. ሲነሱ የሕዝብ ብሶትን ተመርኩዘው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለዚኽ ጥያቄው የግድ ለምን ተነሱ ከሚለው ይበልጥ መታየት ያለበት አንደኛ ለዚያ የሕዝብ ትክክለኛ ብሶት ቀጥተኛና ብቸኛ ተጠያቂ የሆኑት ብልሹ ሥርዓቶች መሆናቸው እየታወቀ ጥያቄው ተለጥጦና ተዛብቶ ለብሶቶቹ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊነት ወይም አንድነት እንደሆነ ተደርጎ መቅረቡ እና ሁለተኛ ያ የሕዝብ ብሶት የተወሰኑ ቡድኖች ጉዳይ ብቻ ተደርጎ መታየት የሌለበትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ጉዳይ መሆኑ፣ ሁሉም ተባብሮ እንዲያስወግደው አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን ዓላማችን ብለው የተነሱበት፣ መስዋዕትነት የከፈሉበትና እየከፈሉበት ያለ የጋራ ዓላማ እንደሆነ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ፣ ወደ-ኋላ ያየና ዜጎችን የሚከፋፍል፣ አገር አንድነትም የሚንድ በመሆኑ ነው፡፡

እዚኽ ላይ ልብ ሊባል የሚገባ ሌላ ጉዳይ ያለ ይመስለኛል፡፡ በመጀመሪያ ስለ-ድርጅቶቹ ሲነሣ የግድ በውስጡ ስለታቀፉ ግለሰቦች/ዜጎች ሣይሆን ያ ድርጅት ቆምኩበት ስለሚለው እምነትና ስለሚከተለው ፍልሥፍና እንደሆነ ያጤኗል፡፡ ብዙዎች ወደ እነዚኽ ድርጅቶች ሲገቡ በቦታው የተሻለ አማራጭ ከማጣትና በወቅቱ ባሉ የተለዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደሆነም ሊታሰብ የሚገባው ይመስለኛል፡፡ እንዲሁም በ"ነፃ-አውጭ" ድርጅቶችና በአርነት እንቅስቃሴዎች መኻል ያለውን ልዩነት ማጤኑ ተገቢ ይሆናል፡፡ አንድ ድርጅት ቋንቋን ይሁን ዘርን ወይም ሐይማኖትን መሠረት አድርጎ በአንድ የአገር ክፍል ውስጥ የሚኖርን ሕዝብ "ነፃ አወጣለሁ" ብሎ ሲነሣ ቀጥተኛ ትርጉሙ ያ በስሙ ጥያቄው የተነሣለት ሕዝብ ችግሩ አንድነቱ (ኢትዮጵያዊነቱ) እንደሆነ፣ ያም በመሆኑ ከቀሩት በዚያ አገር ውስጥ ከሚኖሩ ወገኖቹ ጋር አብሮ መኖር አይችልምና ይለይ፣ ይገንጠል ማለት መሆኑ ነው፡፡ በአንፃሩ በአገሪቱ ላለው ዜጋ ሁሉ (ለጠቅላላው ሕዝብ) ሁለተናዊ መብቶች መከበር፣ ለእኩልነትና ለፍትኅ ከሚታገሉ አገር-አቀፍ (ብሔራዊ) ድርጅቶች ውጪ ለተወሰነ የሕዝብ ክፍል አርነት የሚታገሉ ድርጅቶች ሊኖሩ የመቻላቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይኽ ደግሞ ብዙ አድልዖ ለረጅም ጊዜ ተንሠራፍቶ ለቆየባትና ዜጎች በግለሰብም ይሁን በወል እኩልነታቸው ያልተረጋገጠበት ብቻ ሣይሆን እጅግ ለከፋና በጣም ኋላ-ለቀረ ጭቆና የዳረገ፣ በኅብረተሰባችን ልዩ ልዩ ክፍሎች መኻል ያለው ግንኙነትና ዝምድናም በጣም የተዛባና ያልተስተካከለ ሆኖ በቆየባት አገራችን አዲስ ሆኖ ሊታይ የሚገባ አይመስለኝም፡፣

ይኽ አባባል ለብዙዎች "አልሸሹም ዞር-አሉ" ዓይነት ሆኖ ሊገኝ ቢችልም የነዚኽ ዓይነት ድርጅቶች ምንም እንኳን አደረጃጀታቸው ቋንቋን ወይም ብሔረሰብን/ጎሣን መሠረት ያደረገ ሊሆን ቢችልም፣ **አንደኛ ችግራቸው የአገሪቱ አንድነትም ይሁን የሕዝቡ የተሣሰረ የጋራ ዕድል (ኢትዮጵያዊነት)፣ ትግላቸውም ከዚሁ አንድነት ጋር ሣይሆን ለጭቆናው ተጠያቂ ከሆነው ሥርዓት ጋር** እንደሆነ አምነው የተነሱ እና ዓላማቸውም ያ ሕዝብ ከቀረው የአገሪቱ ሕዝብ ለየት ያሉ ሊስተናገዱና ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ማለት በእሱነቱ/በማንነቱ (ኦሮሞ ስለሆነ፣ አማራ ስለሆነ፣ አኙዋክ ስለሆነ፣ ወዘተ.. ብቻ) የደረሰ/የሚደርስ በደልም ሆነ አድልዖ ልዩ ትኩረትን በሰጠ መልኩ እንዲታይና መፍትኄ እንዲፈለግለት ጫና ለማድረግ ነው፡፡ ለምሣሌ በአማራ፣ በአኙዋክ፣ በጉራጌ፣ በኦሮሞ፣ ወዘተ.. ስም በእነሱነታቸው/ በማንነታቸው ብቻ የሚሰነዘርባቸውንና የሚደርስባቸውን በደልና ጥቃት ለማስወገድ፣ አንድነታችን ፍፁም እኩልነት ላይ እንዲቆምና ፍትኅ እንዲሰፍን የቆሙ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄዎች እንደ-ማለት ነው፡፡

ሁለተኛ የእነዚኽ ኃይሎች እንቅስቃሴ የመገንጠል ጥያቄ እንዳነሱ ክፍሎች በመሣሪያ ኃይል የተደገፈ አይደለም። ያም ስለ-ሆነ ልዩነቶች በደም አጥር ሣይደነድኑና እየመረቀዘ የሚሄድ የቂም-በቀል አዙሪት ውስጥ ሣይገባ ለችግሮች በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረግ ውይይት ሰላማዊ መፍትኄ ለማስገኘት የተሻለ ዕድልን የሚሰጥ ነው። በአንፃሩ የመገንጠል ዓላማ ያነገበ ድርጅት ጥያቄው በትጥቅ ትግል የታጀበ መሆኑ እንደ-አይቀሬ ሊወሰድ የሚችል ጉዳይ መሆኑን ልብ ይሏል። ሆኖም በዚኽ መልኩ በተደራጁና ለእኩልነትና ለፍትኅ በቆሙ ክፍሎችም ቢሆን አሉታዊ ገፅታዎች እንዳሉ ሊጤን ይገባዋል። እንደ-ሁኔታው በቀላሉ ወደ-ከረረ ፖለቲካዊ ብሔረሰበኝነት የመንሸራተት አደጋ የሚያንዣብብባቸው እንደሆነም ይገነዘቧል። እንዲሁም በተለይ በአሁኑ ጊዜ በአለው የአገሪቱ የፖለቲካ ብሔረሰበኝነት/ጎሠኝነት እንደ-ዘይቤ በተወሰደበት ሁኔታ አገዛዙ የራሱን ዕድሜ ለማራዘም በቋንቋ ቡድኖችም ይሁን ለለውጥ በቆመው ጎራ መኻል ይበልጥ ክፍፍልን ለመፍጠር የሚያስችለውን ዕድል የሚፈጥርለት እንደ-ሆነም ሊዘነጋ አይገባል።

ይሁንናም እነዚኽ ወገኖች በግልጥ የመገንጠል ዓላማን ይዘው ከተነሱ ክፍሎች እኩል ሊታዩ የሚገባ አይመስለኝም። በነዚኽ ወገኖችና በአንድነት ኃይሎች መኻል ለተወሰነ የሽግግር ሂደት ለጋራ ልዕለ-ግብ ትብብር ማድረግ ይቻላል የሚል እምነት አለኝ። “ለተወሰነ የሽግግር ጊዜ” ያልኩበት ምክንያት ያ ዓይነት አደረጃጀት ካለው የተለጣጭነት ባኅሪ አኳያ አቅጣጫውን ለመቀየር ካለው አደጋ፣ እንዲሁም ፖለቲካዊ ገጽታውን ይዞ በዘላቂነት መቀጠል ከሚያስከትለው ኅብረተሰብን የመከፋፈልና ሕዝባችን እንደ-አንድ አገር ዜጋ እንዳያስብ፣ ተከባብሮና ተደጋግፎም ለጋራ መጻዒ-ዕድሉ በጋራ እንዳይቆም እክል ለመሆን ያለውን ዕድል ህሣቤ ውስጥ በማስገባት ነው። ስለ-ሆነም፣ ከነዚኽኞቹ ኃይሎች ጋር የሚደረግ የመሸጋገሪያ ትብብር ለኅብረተሰባችን በመተማመን ላይ የተመሠረተ ብሔራዊ-መግባባትን ለማስገኘት ለሚደረገው ጥረት ከሚኖራቸው ሚና አኳያ ይሆናል። የነዚኽ ቡድኖች እንደ-ድርጅት ያላቸውን ዕድሜ የሚወስነው በአገሪቱ የሚፈጠረው አመችና አስተማማኝ የፖለቲካ ሁኔታ ሊሆን ቢችልም፣ የዴሞክራሲያዊው የአንድነት ኃይል ይዞታም ከቀረው ጋር በሂደት ተዋውጠው (ተዋኅደው) የመክሰም ወይም የመጎልበት ዕድልን ሊፈጥርላቸው ይችላል።

ለአርነት ሣይሆን “በነፃ-አውጭነት” እምነት የተደራጁ ድርጅቶች የአንድን አካባቢ ሕዝብ ብሶት የአጠቃላይ የአገሪቱ ዜጎች ብሶት አካል እንዳልሆነ በመቁጠር “ለኛ ሕዝብ እኛ ብቻ ነን የምናውቅለት” ዓይነት ጠባብ እንቅስቃሴ የሚመራው በአብዛኛው ፊደል በቆጠረውና “ነቃ” በተባለው የልኂቃን የኅብረተሰብ ክፍል ነው። ይኽ የሥልጣን ፍላጎት ጥንውት አጥብቆ የሚፈታተነውና ጊዜኛ የኅብረተሰብ ክፍል፣ የዚኽ ዓይነት ፖለቲካዊ ብሔረሰብን/ጎሣንና ሐይማኖትን መሠረት አድርጎ የሚነሣ እንቅስቃሴ በተፈጥሮው ተለጣጭነት የሚያጠቃው ከመሆኑ ጋር ትግሉ በዋናነት በትጥቅ (በመሣሪያ) የሚደገፍ ስለሚሆን አጋ በለዩት መኻል ብቻ ሣይሆን ሰላማዊው ሕዝብ ላይ የደም መፋሰስን የሚያስከትልና ያም ቅራኔዎች እየተካረሩ፣ የቂም-በቀለኝነት አዙሪቱ እየሰፋ እንዲሄድ ከማድረጉ ጋር ሲጣመር በሂደት ሌሎች ከውጭም ከውስጥም የሚፈልቁ ተጽዕኖዎች እየተጨመሩ በቀላሉ አቅጣጫውን እየቀየረና አሉ የተባሉ ልዩነቶች እየባሱና እየተካረሩ እንዲሄዱ፣ አዳዲሶችም እንዲያብቡ የሚያደርግ ነው። ውጤቱም እስከ-አሁን በዓለም ዙሪያ ባለው ልምድ እነዚኽ የችግሮች ሁሉ መፍቻ ኃይልና ጉልበት ብቻ የሚመስላቸው ታጣቂ ቡድኖች “ቆምንለት” በሚሉት ሕዝብ ላይ የባሰ አፋኝና ጨቋኝ ሥርዓት የሚጭኑበትና እራሣቸውም የለየላቸው አምባ-ገነኖች እንዲሆኑ ሁኔታዎችን የሚያመቻች አደገኛ አሠላለፍና አካሄድ ነው።

**የሆነ-ሆኖ የአገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን በነዚኽ የሕዝብን ብሶት የግላቸው ብቻ አድርገው በሚመለከቱ እና ኋላ-ቀርና አምባ-ገነን ሥርዓቶችን ሣይሆን ኢትዮጵያን፣ ኢትዮጵያዊነትና አንድነቷን ለብሶቶቹ ተጠያቂ ባደረጉ ድርጅቶች ላይ ያላቸው የራሣቸው ብሶት 'እናንተ ብቻ ሣትሆኑ እኔም የጉዳዩ ባለቤት ነኝ፣ በየትም ቦታ ለሚገኘው ወገኔ መብቶች መከበር መታገል ኃላፊነቴና ግዴታዬ ነው፣ የአገራችን አንድነትና ኢትዮጵያዊነት የችግሮቻችን መንስዔ አይደሉም' የሚል ነው።**

የትም ይሁን የት ለሰብዓዊ ክብርና መብት የሚደረግ ትግል ሊደገፍ ይገባል። ቀደም-ሲል ለመጥቀስ እንደ-ሞከርኩት ኢትዮጵያ የሁሉም፣ በየትኛውም ቦታ የሚኖሩ ዜጎቿ ድምር ውጤት በመሆኗ፣ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል የሚገኙ ዜጎች እኩልነት ካልተከበረ፣ መብቶቻቸው ካልተረጋገጡ የማንኛውም የአገሪቱ ዜጋ እኩልነትና መብት አለ-መከበሩ ማለት ስለ-ሆነ፣ የሁሉም ዜጎቿ ሙሉ መብቶች መከበርና እኩልነታቸው ሣይሸራረፍ እንዲረጋገጥ መታገል የሁሉም፣ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ዜጋ ሁሉ፣ የተናጠልም የጋራም ግዴታና ኃላፊነት ነው። በአጋዴን የሚገኙ ዜጎች መብት እንዳይረገጥ፣ የሚደርስባቸው ግፍ እንዲቆም፣ የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ከትውልድ ቦታው ተነቅሎ ጨርሶ ተፈናቃይና የበይ-ተመልካች መሆኑ እንዲቆም፣ በጋምቤላ የአኙዋክ ብሔረሰብ ኢትዮጵያውያን ላይ ለደረሰው ጭፍጨፋ ተጠያቂዎቹ ለፍርድ እንዲቀርቡና ፍትኅ

እንዲገኝ፣ ወዘተ.. መታገል የሁሉም ኢትዮጵያዊ፤ የትግሬውም፣ የኦሮሞውም፣ የአማራውም፣ የሁሉም ኃላፊነትና ግዴታ እንጂ የኦጋዴን፣ የጋምቤላ ተወላጅ፣ ያውም አጥንት በቆጠረና ጎሠኝነትን መሠረት ባደረገ መልኩ ሊሆን አይገባም:: እዚኸ ላይ ነው በኅብረ-ብሔረሰብ (አገር-አቀፍ) የሚደራጁና በፖለቲካ-ብሔረሰበኝነት/ጎሠኝነት የሚደራጁ መኻል የሚኖረው የአስተሣሰብና የፖለቲካ እምነት ልዩነት:: የመጀመሪያዎቹ በመርኅ ደረጃም ሆነ በተግባር እንደሚታየው ድርጅታቸው ለማንኛውም የአገሪቱ ዜጎች ለአባልነት ክፍት ነው:: የሁሉም ብሶት ብሶታቸው፣ ችግሩ ችግራቸው“ በደሉ በደላቸው፣ ትግሉም ትግላቸው፣ የወደፊት ዕድሉም የጋራ ዕድላቸው ነው:: የሚታገሉትም ለዜጎች ሰብዓዊ ክብርና መብት መከበርና ማንም ዜጋ ምንም ቋንቋ ይናገር ምን፣ ምንም እምነት ይከተል ምን፣ የትም አካባቢ ይኑር የት፣ ያታን፣ ዕድሜንም ሆነ ሙያን ሣይለይ ፍትኅና እኩልነት ለሁሉም ያለ ምንም አድልዖ እንዲሠራ ለማድረግ ነው:: በሁለተኞቹ ድርጅቶች በኩል ማንኛውም የድርጅታቸው አባል “የነሱ” ተወላጅ ሊሆን መርጉ የግድ ይላል:: ብዙውን ጊዜ አባልነት ከ“ተወላጅነት” ወርዶም የእነሱን እምነት መከተልን ይጠይቃል:: ሁሉም የትግራይ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ሕወሓት፣ የኦሮሞ ተወላጅ የሆነ ሁሉ ኦነግ፣ ወዘተ እንዳልሆነና ሊሆንም እንደማይችል ሁሉ ማለት ነው:: ለነዚኸ ክፍሎች ብሶታቸው የነሱ ብቻ፣ በደሉም ሁሉ በነሱ ላይ ብቻ የደረሰ፣ ወዘተ. ተደርጎ ነው የሚወሰደው::

ዘርን፣ ሐይማኖትንና ብሔረሰብን/ጎሣን መሠረት ያደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉ የአግላይነት ተፈጥሮአዊ ባኅሪን የተላበሱና በ“እኛና እነሱ” አስተሣሰብ የተገሩ በመሆናቸው “እነሱን ያልመሰለውን” ወይም የነሱን የፖለቲካ ፍልሥፍናና እምነት የማይከተለውን እንደ ጠላት የሚያይና በዚያም የሚፈርጅ በመሆኑ ቢያንስ ለሁሉም ክፍት ያልሆኑና እኩል ማስተናገድ የማይችሉ ናቸው:: እነሱን ብቻ “ለሚመስሉ” የተከለለና በዚያ አጥር የታቀቡና ከዚያ ውጭ ላሉ ዝግ በመሆናቸውም እንደዚኸ ዓይነት ድርጅቶች “ለተወሰኑ አባላት ብቻ” የተፈቀዱ (Exclusive Clubs) ናቸው የምለውም ለዚኸ ነው:: በተለይም በዚኸ መልክ ተደራጅተው ዓላማቸውን እግቡ ለማድረስ የታጠቀ ትግል የሚያደርጉ ክፍሎች “ፍልሚያው” በደም መፋሰስ ስለሚታጀብ የልዩነት አጥሮችን የሚያፈርሱ ሣይሆን እንደሚያደነድኑ የታወቀ ነው::

በዚኸ “የእኛና እነሱ” ዘይቤ የተደራጁ በመሆናቸውም ነው እነ-መለስ ዜናዊና ድርጅቱ ሕወሓት ሃያ-ዓመት በአገራዊ ሥልጣን ላይ ሲቆዩ እራሣቸውን ከዚያ ጠባብ አመለካከት ማውጣት አቅቷቸው፣ ኢትዮጵያዊነት እየተናነቃቸው፣ የአገር ዳር-ድንበር ቆርሰው ለባዕዳን ሲሰጡ ቅም የማይላቸው፣ አገራዊ ተቋማትን ጭምር እያፈረሱ “በራሣቸው” የድርጅት አባላት፣ ያም ካልተገኘ አጥንት ተቆጥሮ በጎሠኝነት መንፈስ የተቃኘ ተራና ኋላ-ቀር ተግባር ላይ የተሠማሩት፣ እና ያገኙትን አገር የመምራት ክብርና ዕድል አመስግነው በፀጋ ከመቀበልና ሁሉንም ዜጎች በእኩል ዓይን ማየት አቅቷቸው የሕወሓት ጠባብ ጎሠኛ መንግሥት ከመሆን ለመላቀቅ ያልቻሉት:: ስለ-ሆነም 'ከአባባሉ ምግባሩ' እንዲሉ ያ ዓይነት የነ-አቶ መለስ አድሎያአዊና አግላይ ፍልሥፍናና ይዞታ እንጂ አንዳንዶች እንደሚሉት ትውልዳቸው ከትግራይ ስለ-ሆነ አይደለም ኢትዮጵያውያን ገላቸውን ሰደውና ሙሉ አመኔታቸውን ሰጥተው የኛ የሁላችንም መንግሥት ነው ብለው ለመቀበል፣ በኢትዮጵያ ስም የሚሠራን ሥራ ሣይቀር ከነሱ ሲመጣ ያን ያኸል በሞቀ ስሜት ለማስተናገድና እንዳለ በቀና መንፈስ ለማየት የሚከብዳቸው፣ ልባቸውንም ከፍተው በጉጉት ለመቀበል የሚቸገሩት::

## ዝንታለም የመበለጥ አባዜ የተጠናወተውና አቅሙን አኮስሶ የሚያየው የአንድነት ኃይል፤

መቸም ጊዜው ነገሮችን ሰክኖ ማየት የማይቻልበት ሆኗል መሰለኝ ይኸ “አዲስ” አቀራረብ በተወሰኑ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ መልካም ዜና ከመወሰድ ጀምሮ ቅጥ-ያጣ “የምሥራች” አብሣሪ ዜናዎችም ሲሰራጩ ተስተውለዋል:: ይኸንን ስብጥርጥሩ የወጣ አደገኛ አሠላለፍም ከ 1931 እስከ 1941 የዘለቀውን የጃፓንን ቅኝ-ገዥ ወረራ በጋራ ለመመከት በሻንጋይ-ሼክ በተመራው የኮሚታንግ ብሔረተኛ መንግሥትና እሱኑ ለመጣል ይታገል በነበረው በማኦ በተመራው የቻይና ኮሚዩኒስት ፓርቲ መኻል ከየግል ድርጅቶቻቸው አብልጠው ላይዋት የጋራ አገራቸው ሲሉ ካደረጉት ጊዚያዊ መተጋገዝ ጋር ሊያመሣስሉ የሞከሩም አጋጥሞኛል:: እነኛ ሁለት ኃይሎች (የቻይና ኮሚዩኒስት ፓርቲና የሻንጋይ-ሼክ ብሔረተኛ መንግሥት) በቻይና አንድነት ላይ ጥያቄ ሊኖራቸው ቀርቶ ቀናዒ ከመሆን የወረደ አቋም አልነበራቸውም:: “የተባበሩት መንግሥታት በሸዓብያ ላይ ያሣለፈውን የማእቀብ ውሳኔ ተሰልፈን እንቃወም፣ ... ኦነግ ወያኔን ለመጣል ከኢትዮጵያውያን ጋር እተባበራለሁ ብሎ መግለጫ አወጣ፣ .. እስካሁን ከኛ ጎን ቆሞ የማያውቀው ኦብነአግ ባዘጋጀነው ፀረ-ወያኔ ሰልፍ ላይ ተገኘ፣ ወዘተ፣ ወዘተ.. ” የሚሉ አባባሎች መደመጥ ከጀመሩ ውለው አድረዋል:: ይኸ ግራ-የተጋባና መላ-ቅጡ የጠፋ አካሄድ ምንጩ ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ ያነሱና በነገሩ የተገረሙ፣ አልፎም “አንጀታቸው ያረረና ቆሽታቸው የደበነ” አገር-

ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያውያን መኖራቸው አልቀረም:: ለነገሩ የሚገርመው ኢትዮጵያዊ ነን ባሉ ወገኖች የሚታየው ተላላነት እንጂ ከአለው አጠቃላይ ዓለም-አቀፍ፣ የአካባቢና የውስጥ ሁኔታ አኳያ ሲታይ የእነዚያ ኃይሎች ይኸንን "አዲስ ደራሽ" አቋም መያዛቸው ሊጠበቅ የሚገባው ነው::

አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ኦነግና ኦብነአግ የመሰሉ ድርጅቶችን የሚያዩአቸው እነኝኸ ቡድኖች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ላይ ባላቸው አሉታዊ እምነት ሣይሆን እነሱ አለን በሚሉት "ፀረ-ወያኔ" ቀጭን አቋም ብቻና እነኝኸ ቡድኖች የሕወሓት/ኢሕአዴግን አገዛዝ ለማስወገድ በሚደረግ ጥረት ላይ ሊኖራቸው ይችላል ብለው ከሚያስቡት "አስተዋፅዖ" አኳያ እንደሆነ ይታወቃል:: የተወሰኑ ወገኖች ደግሞ እነዚኸን ቡድኖች የሚያዩአቸው "እንወክለዋለን" ከሚሉት የሕብረተሰባችን ክፍል ጋር በማጣመርና እነሱንም የዚያ እነሱ "የእና" የሚሉት የኅብረተሰባችን ክፍል "ተወካይ" አድርገው ነው:: ከዚያም አልፈው በእነዚኸ ድርጅቶች ላይ የሚደረግን ትችት እነሱ "እንወክለዋለን" በሚሉት ሠፊ ሕዝብ ላይ እንደሆነ አድርገው ይቆጥሩታል:: ከዚያ የተሣሣተ አመለካከት በመነሣትም እነዚኸን ቡድኖች ከመንገድ በወጣ መልክ እሹሩሩ ማለትና ማባበል ደረጃ የደረሰ አቀራረብ ላይ ብዙዎችን እንደጣላቸው የሚታይ ነው:: በሁለቱም በኩል ያለው ግምት ግን የተሣሣተ ነው ባይ ነኝ:: **የመጀመሪያውን ነጥብ ወደ-ኋላም የምናየው ቢሆንም ያለውን አገዛዝ ለመለወጥና በአገራችን ሁሉም አትራፊ ሊሆንበት የሚችል ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን አገር-ወዳዱና ዴሞክራቱ ኃይል አቋሙን ካስተካከለና አቅሙን በሚገባ ከተጠቀመ የነዚኸን ፀረ-አንድነት ኃይሎች እርዳታም ሆነ ትብብር አያስፈልገውም:: ጋፍኛ ከነሱ ጋር የሚደረግ "ትብብር" የሚጎዳው የጋራ ትግሉንና የሚጠቅመውም የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ነው::** ሁለተኛ እነሱ "ቆመንለታል" ብለው በስሙ የተደራጁ እነኝኸ ቡድኖች ያንን የኅብረተሰብ ክፍል ይወክላሉ የሚያሰኝ መመዘኛ የለም:: ከዚሁ ጋር መታሰብ የሚገባው በዚኸ ስሌት ከሆነ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ቀርቶ በተለይ በየ አገር-አቀፍ ድርጅቶች ያሉ፣ ለአጠቃላዩ የአገሪቱ ሕዝብ የሚታገለውና እነዚኸ አናሣ ኃይሎች "የእኛ" ከሚሉት ኅብረተሰብ የወጣውን ሥፍር-ቁጥር የሌለው ኢትዮጵያዊ "ተሣስታችኋል"፣ ለዚያ አካባቢ ሕዝብ አትታገሉም ማለትም ይሆናል::

ለመሆኑ እነዚኸ ኃይሎች ያላቸው መሠረታዊ አቋምና ታሪካቸው አሁን ከሚሰበከው "ለአገር ጠቃሚ" ሆኖ መገኘት ጋር ይጣጣማል ወይ?

እንደሚታወቀው የ"ኦጋዴን ነፃ-አውጭ" ነኝ ብሎ ነፍጥ አንስቶ የሚታገለው ቡድን ጠቡ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ጋር እንደሆነ ***"የኢትዮጵያ ሕገ-ወጥ ቅኝ ግዛት የሆነውን አገራችንን ከቅኝ ገዥዋ ከኢትዮጵያ ነፃ ለማውጣት"*** ነው ሲል ከሌላ ሣይሆን በፕሮግራሙ ላይ ዓላማየ ብሎ በግልጥ ባስቀመጠው ያረጋገጠው ሃቅ ነው:: ***"በአፍሪቃ የመጨረሻዋ ቅኝ ተገዥ ዓረባዊት አገር" የሆነችውን "ኦጋዴንያ" "ነፃ ለማውጣት"*** እታገላለሁ የሚለው ይኸ ቡድን ዓላማውን ለማሣካት በሚያደርገው የመሣሪያ ፍልሚያም ከሸዓብያ ጀምሮ ከሩቅም ከቅርብም ባሉ የለየላቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች በቀጥታና በተዘዋዋሪ እንደሚረዳም ይታወቃል::

ሶማሊያ ነፃ ከወጣችበት ጊዜ አንስቶ አንድ-አምስተኛ የሚሆነውን የኢትዮጵያ ክፍል "ኢትዮጵያ የወሰደችብንን አምስተኛዋን ኮከብ" አናስመልሣለን በሚል የተስፋፊነት እምነት በጉልበት ለመንጠቅ እብሪተኞቹ የሶማሊ መሪዎች ሰላም-ወዳዷ አገር ላይ ድንበር ጥሰው ተደጋጋሚ ወረራ በማድረግ የንፁኃን ዜጎቻችንን ደም በከንቱ ማፍሰሣቸው፣ ማፈናቀላቸውና ንብረታችንን ማውደማቸው አይዘነጋም:: የመጨረሻው ይፋዊ ጦርነት በመደበኛው የሶማሌ ዘመናዊ ጦር ከመጀመሩ በፊት ግን በብዙ አሥርተ-ሽህዎች የሚቆጠሩ "የምዕራብ ሶማሌ ነፃ-አውጭ" እና "ሶማሌ አቦ" የተሰኙ ቡድኖችን አደራጅቶ በቀዳሚነት ማሠለፉም ይታወቃል:: እነዚያ ኃይሎችም የዚኹ ተስፋፊ እቅድ ግንባር-ቀደም ዘማች በመሆን ኢትዮጵያውያንን በራሣቸው አገር ላይ እንደ-ከብት እያረዱና ይኸ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የማይችል አሰቃቂ ግፍ እየፈጸሙ ወራሪውን ጦር ድሬ-ዳዋ በር ድረስ መርተው አምጥተዋል:: እነኝኸ ወንጀለኛ አምስተኛ-ረድፈኞች አለቃቸው ወራሪው የሰይድ ባሬ ጦር በኢትዮጵያ ሕዝብ የተባበረ ክንድ አይቀጡ-ቅጣት ተቀጥቶና አዋራጅ ሽንፈትን ተቀብሎ ተጠራርጎ ከኢትዮጵያ ምድር ከወጣ በኋላ እንደሚታወቀው ሶማሌም መንግሥት-አልባ ስትሆንና ሕዝቧ ለአሣዛኝ ትርምስ ሲዳረግ፣ ወቅቱ ደግሞ በታሪክ አጋጣሚ ብሔራዊ ስሜትና አገራዊ ኃላፊነት የራቃቸው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ገዥዎች ሥልጣን መያዝ ጋር ስለተገጣጠመ፣ እነዚያው ገንጣይ-አስገንጣይና አፍራሽ ኃይሎች በአዲስ መልክ ተደራጅተውና የዕብሪተኛው ሰይድ ባሬን የጦር አበጋዞች መሪ አድርጎ ብቅ ማለቱ ይታወቃል::

አዲሶቹ የኢሕአዴግ ባለ-ሥልጣኖችም የሰይድ ባሬ መንግሥት ላደረገላቸው ትብብርና እርዳታ ውለታ ለመመለስ በሚመስል እርምጃ ይኸ በሰይድ ባሬ የባሕር-ኃይል አዛዥ የሚመራ ድርጅት በ"ሽግግሩ" ወቅት "የክልል መንግሥት" እንዲሆን ሁኔታዎችን እንዳመቻቹና እንደረዱም ግልጥ ነው::

**ይቀጥላል......**